


በ: ዮራም ታሃርሌቭ
ምሳሌዎች: ያኒቭ ሮተም
הוֹצָאָה: מודן
የእድሜ ክልል: ቅድመ ትምህርት ቤት

קְרִיאָה

ምክር ለቤተሰባዊ ንባብ

በመፅሃፍ ውስጥ ያለው ተደጋጋሚ ዓረፍተ ነገር ልጆች ታሪኩን እንዲከታተሉ፣ በንባብ ንቁ እንደሆኑ እንዲሰማቸውና የጋራ ልምዳቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳል። የተደጋገመውን ዓረፍተ ነገር በልዩ ድምጽ ማንበብ፣ የእጅ ምልክቶችን መጨመር ወይም የንባብ ፍጥነትን መለወጥ ይችላሉ። በዚህ መንገድ ወደ እርሱ በመጡ ቁጥር ሴትና ወንድ ልጆች ከእርስዎ ጋር በመገናኘታቸው ደስተኞች ይሆናሉ።

שִׂיחָה

ይሄንም ያንንም

ይሄንም ያንንም የመፈለግ አዝማሚያ በልጆች ሕይወት ውስጥ የታወቀ ሁኔታ ነው – ከልጆችዎ ጋር መነጋገርና መጠየቅ ይችላሉ:- ወይዘሮ በጻልኤል የያዙትን እቃዎች ሁሉ ለምን ጣለች? የገዛችውን ሁሉ የምትፈልገው ይመስላችኋል? ይህ ሲከሰት ምን የተሰማት ይመስላችኋል? ተመሳሳይ ነገር አጋጥሞዎታል? ወይዘሮ በጻልኤል ምን ?እንድታደርግ ይመክራሉ

מִשְׁתָּק

የሚገዙ ነገሮች ዝርዝር

ታሪኩን ደጋግመው ካነበቡ በኋላ እየተዝናኑ ይፈትኑ፡- ወይዘሮ በጻልኤል በቅደም ተከተል የገዛቻቸውን ነገሮች ማን ?ያስታውሳል

מִשְׁתָּק

!ጥንቃቄ! እንዳትወድቁ

ምን ያህል አሻንጉሊቶችና እቃዎች ሳይወድቁ በእጆችዎ ውስጥ መያዝ ይችላሉ? በታሪኩ ተነሳሽነት አሻንጉሊቶችን፣ መጫወቻዎችን (የማይሰበሩ)፣ ትራሶችንና ለስላሳ እቃዎችን ከቤት ውስጥ መሰብሰብና ከአንድ ነጥብ ወደ ሌላ መንገድ ማዘጋጀት ይችላሉ። አሁን እያንዳንዱ ሰው ተራ በተራ በተቻለ መጠን ብዙ እቃዎችን በመያዝ በተሠየመው መንገድ አብሮ ይራመዳል – የወደቀ ነገር አለ? ወደ መጀመሪያው ይመለሱ።

מִשְׁתָּק

!ምን ያህል መልካም ነው

ምን ነገር መልካም ያደርግልዎታል? በቀኑ መጨረሻ ከመተኛቱ በፊት ‘‘ምን ያህል መልካም ነው’’ የሚለውን ጨዋታ መጫወት ይችላሉ – እያንዳንዱ ሰው ዛሬ ስለተፈጠረ ጥሩ ነገር ወይም ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ስለሚያደርግ ነገር ይናገራል።

שֵׁמַע

QR ኮድ

ኮዱን ስካን ያድርጉና ገጣሚና ደራሲ ዮራም ታሃርሌቭ ታሪኩን ሲያነብ ማዳመጥ ይችላሉ።

הַשְׁרָאָה

ፒንተረስት

[ለተጨማሪ ስራዎች፣ መዝሙሮችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ]

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org